# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የትምህርት ቢሮ

## Central Ethiopia Region Government

## Bureau Of Education


ቀን/Date: ጥቅምት 18 ቀን 2017

ቁጥር/Ref.No: 101/ለ30-591/ለ7/35

ለ ሀዲያ ዞን/ልዩ ወረዳ ትምህርት መምሪያ/ጽ/ቤት

በያሉበት

**ጉዳዩ፡- የአቻ መምህራን ትይዩ አስመልክቶ ሰርኩላር ስለማስተላለፍ፤**

የትምህርት ቤት አመራር ሪፎርም ሲደረግ በወጣው የትምህርት ቤት አመራር የውድድር ማስታወቂያ የትምህርት ዝግጅት ወይም የሙያ መስመር ወይም ልምድ ባለማሟላታቸው ወይም የውድድር መስፈርቶቹ የሚጋብዛቸው ባለመሆኑ ወይም በመደበኛ ፕሮግራም ትምህርት እየተከታተሉ በመሆናቸው ወይም በፈቃደኝነታቸው ወይም በውድድሩ ባለመመረጣቸው ከመስከረም 30/2017 ዓ/ም ጀምሮ ከሱፐርቫይዘርነት/ ከርዕሰ መምህርነት/ ከምክትል ርዕሰ መምህርነት እንዲነሱ የተደረጉ የቀድሞ የትምህርት ቤት አመራሮች ከጥቅምት 1 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ ወደ መምህርነት ሙያ ሲመደቡ የአቻ መምህራን ትይዩ ደመወዝ አፈፃጸም ላይ እየቀረቡ ያሉ የአፈፃጸም ጉድለቶችን ለማረም ሰርኩላር ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ነባር የትምህርት ቤት አመራሮች ወደ መምህርነት ሙያ ሊመደቡ የሚችሉት በትምህርት ቤቶች በሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ተመርቀው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፡፡ በዚሁ አግባብ ሲመደቡ የአቻ መምህራን ደመወዝ ትይዩ የሚፈጸመው ህጋዊ በሆነው የትምህርት ዝግጅታቸው በሰንጠረዡ በተመላከተው አግባብ የስራ ልምዳቸው በሚያደርሳቸው የዕድገት መሰላል ላይ እንዲያርፉ በማድረግ ብቻ በጥንቃቄ እንዲፈጸም እናሳስባለን፡፡

| ተ/ቁ | በመምህርነት፣ በርዕሰ መምህርነት፣ በምክትል ርዕሰ መምህርነት እና በሱፐርቫይዘርነት በእያንዳንዱ የተገኙ ልምዶች ተደምረው የሚገኘው ልምድ | የመምህራን የደረጃ ዕድገት መሰላልና መነሻ ደመወዛቸው | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የዕድገት መሰላል | በዲፕሎማ የትም/ዝግጅት መነሻ ደመወዝ | በመጀመሪያ ዲግሪ መነሻ ደመወዝ | በሁለተኛ ዲግሪ መነሻ ደመወዝ |
| 1. | ከ3-5 ዓመት ከሆነ | መለስተኛ መምህር | 5,358 | 6,193 | 7,071 |
| 2. | ከ6-8 ዓመት ከሆነ | መምህር | 6,193 | 7,071 | 8,017 |
| 3. | ከ9-11 ዓመት ከሆነ | ከፍተኛ መምህር | 7,071 | 8,017 | 9,056 |
| 4. | ከ12-14 ዓመት ከሆነ | ተባባሪ መሪ መምህር | 8,017 | 9,056 | 10,150 |
| 5. | ከ15-17 ዓመት ከሆነ | መሪ መምህር | 9,056 | 10,150 | 11,305 |
| 6. | ከ18 ዓመት በላይ | ከፍተኛ መሪ መምህር | 10,150 | 11,305 | 12,579 |
| 7. | ከሐምሌ 1/2011 ዓ/ም በፊት ከ18 ዓመት በላይ ልምድ የነበራቸው ወይም እስከ አሁን ከ23 ዓመት በላይ ልምድ ያላቸው ከሆነ ብቻ | ከፍተኛ መሪ መምህር | 11,305 | 12,579 | 13,926 |

//ከበጎ ምኞት ጋር//

ተሾመ ኃይሉ ተሰማ

የመምህራን፣ የትም/አመራር እና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

- ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለመምህራንና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ትምህርት ቢሮ